

# 2

# የማያቋርጥ ጦርነት

## 2-1

የክርስትና ሕይወት ትግል የሞላበት ሕይወት ነው። በመንፈሳዊ ሕይወቱ በማደግ ላይ ያለ ማንኛውም ክርስትያን ወደፊት አንድ እርምጃ በተራመደ ቁጥር በዚያው ልክ የሚዋጋው የጠላት ኃይል እየበረታና እየጨመረ ይሄዳል። ይሄ በብዙዎች አማኞች ሕይወት ላይ ደርሶ የታወቀ ቢሆንም፥ በሁላችንም ሕይወት ሊደርስ የሚችል የክርስትና ሕይወት አኗኗር ደንብ መሆኑን ብዙዎቻችን እንረሳለን። በዚህም ምክንያት የጠላትን አመጣጥ፣ ዘንዴውንና ጥበቡ ስለማይገባን ሕይወታችን ምንጊዜም ለጥቃት የተጋለጠ ይሆናል። ሰይጣን ክርስትያን የተባለውን ሁሉ በጣም ይጠላል። ርህራሄና ልስላሴም የለውም። አማኝ በመከራውና በጭንቀቱ የሚያፈሰው ዕንባ ይጣፍጠዋል። ወግቶ ለመጣልም በሚችለው በማንኛውም ዓይነት ድብቅና ግልጽ መሣሪያ ከመጠቀም ወደኋላ አይልም። ገፍቶና ወግቶ ካልጣለ፥ ክፉን ያወራል፤ ያስወራል። “ሰይጣን በክርስትያኖች ላይ ይህን የመሰለ ከባድ ጥላቻ ያደረበት ለምን ይሆን?” ምክንያቶቹ ብዙ ናቸው።

## እግዚአብሔር የሚወዳቸውን ሰይጣን ይጠላል

እግዚአብሔር አማኞችን ይወዳቸዋል። መውደድ ብቻ ሳይሆን እንደ አንድ ዓይኑ ብሌን የሚመለከታቸው ዕንቁዎቹና ደስታዎቹ ናቸው። ሆኖም እግዚአብሔር የወደዳቸውን ሁሉ ሰይጣን ይጠላቸዋል። በዚህ ምክንያት በእግዚአብሔርና በአማኞች መካከል መቀራረብ እንዳይኖር ብዙ ዕንቅፋቶች ለመፍጠር ይሞክራል።

## የፈጣሪያቸውን አምሳል የሚይዙትን ይጠላል

እውነተኛ አማኞች ወደዚህ ወደ አዲስ ሕይወት ሲገቡ የቀድሞ ይዞታቸው ይለወጥና አዲስ ሕይወት ይለብሳሉ። የእግዚአብሔርን የሠሪያቸውንም መልክና ባህሪ መያዝ ይጀምራሉ። በዚህም ሰይጣን ይቀናል። ቀደም ሲል የጀመረው በእግዚአብሔር ላይ ያለው የመረረ ጥላቻ ከብዙ ዘመናት በኋላም ስለአልተለወጠ፥ የክርስትያኖች የእርሱን ባህሪ ይዘው ማደጋቸው ያናድደዋል። እግዚአ ብሔርን የሚመስል መልክና ባህሪ ያለውን ሁሉ ባለው ኃይሉና ጉልበቱ ለመደምሰስ የሚያደርገው ጥረት የለም።

# ከድተውት የወጡትን ሁሉ ይጠላል

ማንኛውም አማኝ አምኖ ወደ አምላኩ ከመምጣቱ በፊት ከሰይጣን ካምፕ ውስጥ ብዙ የቆየ ነው። ታዲያ ከዚያ ብዙ ዘመን ከኖረበት ካምፕ አምልጦ ወደ ክርስቶስ ካምፕ የገባ ኮብላይ በመሆኑ ያ ቀደም ሲል ይገዛው የነበረው ጌታው አሳዶ ወደ መጣበት ለመመለስ ሲሞክር በግልጽ ይታያል።

# መንግሥቱን የሚያናጉበትን ይጠላል

ሰይጣን በተለይ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚበረቱትን ይኸውም አስደናቂ የጸሎት ሕይወት ያላቸውን በአገልግሎት የሚበረቱትን እነዚያን ከማንኛውም ይበልጥ ስለሚፈራቸው አብዝቶ ይጠላቸዋል። ፍርሃቱ እነርሱ እራሳቸው ከእርሱ ካምፕ አምልጠው መውጣቸውን ብቻ ሳይሆን፥ ሌሎች በእርሱ ቁጥጥር ሥር ያሉትን ነፍሳት "በወንጌል ቃል አባብለው ከሥሬ ያወጡብኛል" በማለት ፍርሃት ስለሚያድርበት ነው። ክርስቲያን ከሰይጣን ግዛት አምልጦ ከወጣ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ሙሉ ነጻነት ያለው በመሆኑ፥ በሰይጣን ግዛት ውስጥ አደጋ ያደርሳል ተብሎ ስለሚፈራ፥ ሰይጣን በጥንቃቄ የክርስቲያንን እርምጃ ይጠብቃል። ወደ እግዚአብሔር ዙፋን በጸሎት እያዘወተረ የሚቀርብ ከሆነ በሕይወቱ ማደጉ ስለማይቀር ሰይጣን በጣም ይፈራል። ለዚህ ነው በተለይ ገና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ወጣት የሆኑትን ቶሎ ተስፋ አስቆርጦ ወደኋላ እንዲመለሱ ለማድረግ የሚታገለው። ሰይጣን ከአዋቂነቱ የተነሳ አንድ አዲስ አማኝ አድጎ፣ ሙሉ መንፈሳዊ ሰው ሆኖ ግዛቱን ሳይደፍርበት ገና በሕጻንነቱ ወግቶ ሊጥለው ይሞክራል።

ሙሴ አድጎ የእሥራኤልን ህዝብ ከባርነት ነጻ እንዲያወጣ ቀደም ሲል ያውቅ ስለነበር በሕጻንነቱ ወግቶ ሊጥለው ሞክሮ ሳይሳካለት ቀረ። ክርስቶስንም በሕጻንነቱ ወግቶ ሊጥለው ሞክሮ የወሰደውን እርምጃ እንዳልተሳካለት እናነባለን። በዚሁ መልክ አማኙንም ገና አዲስ ክርስቲያን እያለ ካዳከመው ወደፊት በሰይጣን ግዛት ውስጥ አደጋ ያስከትላል ብሎ አይፈራውም። ሰይጣን በሥጋ ክርስቲያኖችን ወግቶ አደጋ ለማድረስ ይህን ያህል ጉጉት ያለው አይደለም። ምክንያቱም እርሱ ጥቃት ለማድረስ የሚፈልገው ከላይ ያለውን ቀፎ (ሥጋ) ሳይሆን ዘለዓለማዊ በሆነው መንፈሳችን ላይ ነው። በምድራዊ ጦርነት ላይ ተሰልፎ ብዙ ጀብዱ የሠራ ወታደር በጦር ሜዳ ተመትቶ ቢወድቅ ለአገሩ ክብርና ዝና እንጂ ጉዳት አያመጣም። ነገር ግን በጦርነት ላይ ተሰልፎ ገና የአንድ ጥይት ድምጽ ሲሰማ ፈርጥጦ ገደል የሚገባ ወታደር ለአገሩና ለቤተሰቡ ውርደትን ያመጣል። እንዲሁም ክርስቲያን በእምነቱ ጸንቶ ከጠላቱ ከሰይጣን ጋር ሲዋጋ በጦር ሜዳ ላይ በሥጋው አደጋ ደርሶበት ቢሞት ላለበት ለጽድቅ መግሥት ጉዳት ሳይሆን ክብርን ያስገኛል። የጠላትም ሠራዊት በሥጋው ወግቶ ቢጥለው ድል እንዳገኘ አይቆጥረውም።...

**በሚቀጥለው ክፍል፥ መንግሥቱን የሚያናጉበትን ይጠላል የሚለውን የላይኛው ሃሳብ ጨርሰን፥ ታማኝ በትግሉ ለምን እንደሚረታ እንመለከታለን።**

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን!**